የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመላሽ የሚደረግበት ሁኔታን ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 1132/2018

ሚያዝያ፤ 2018 ዓ.ም

<u>አዲስ አበባ</u>

መመሪያ ቁጥር 1132/2018

የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመላሽ ስለሚደረግበት ሁኔታ ለመወሰን የወጣ መመሪያ

ለተጨማሪ እሴት ታክስ ከተመዘገበ ሰው ለሚቀርብ የታክስ ተመላሽ ጥያቄ የስጋት ደረጃን መሰረት ያደረገ የታክስ ተመላሽ አገልግሎት መስጠት በማስፈለጉ፤

የተጨማሪ እሴት ታክስ ነጻ መብት ያለው ሰው ታክሱን በግብይቱ ላይ ከከፈለ በኋላ በተመላሽ ስርዓት ስለሚስተናገድበት ሁኔታ መደንገግ በማስፈለጉ፤

በተለያዩ የስራ ክፍሎች በሚወጣ የተመላሽ ውሳኔ ለሚቀርብ የተመላሽ ጥያቄ ምላሽ መስጠት በማስፈለጉ፤

የቀድሞዉ ተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ከነማሻሻያዎቹ እና ደንቡ የተሻረና በአዲስ አዋጅ እና ደንብ የተተካ በመሆኑ እና አዲሱን አዋጅ መሰረት ያደረገ የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመላሽ መመሪያ ማዉጣት በማስፈለጉ፤

የገቢዎች ሚኒስቴር በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 1341/2016 አንቀጽ 51 በተሰጠው ስልጣን መሠረት ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

ክፍል አንድ

ጠቅላላ ድንጋጌ

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ መመሪያ "**የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመላሽ የሚደረግበትን ሁኔታ ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር** 1132 /2018" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር ለዚህ መመሪያ አፈፃፀም፤

   1/ "**መደበኛ የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመላሽ**" ማለት ለታክሱ የተመዘገበ ሰው የሚያቀርበውን ጥያቄ ተከትሎ በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 1341/2016 በአንቀፅ 48 እና 49 ድንጋጌዎች መሠረት ተመላሽ እንዲሆን የሚፈቀድለት ታክስ ነው፡፡

   2/ "**ለታክስ ተመላሽ የሚቀርብ ማስረጃ**" ማለት ስለ ታክስ ማቀናነስ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በግብአት ላይ ወይም በካፒታል ዕቃዎች እና በንግድ ስራ ሀብቶች እንዲሁም በባለ ልዩ መብቶች ወይም በተመላሽ ስርዓት እንዲስተናገዱ በተፈቀደላቸው ሰዎች የተከፈለ ተጨማሪ እሴት ታክስ ተመላሽ ለማድረግ በታክስ ባለስልጣኑ መቅረብ ያለበት ሰነድ ነው፡፡

3/ **"በብልጫ የተከፈለ ታክስ ማስረጃ"** ማለት በተመዘገበ ሰው በዜሮ የማስከፈያ ልክ ታክስ ለሚከፈልበት ግብይት በዋለ ግብዓት ላይ የተከፈለ የተጨማሪ እሴት ታክስ ወይም የታክስ ተቀናሽ እንዲሆን የተላለፈባቸው የሂሳብ ጊዜያት ካበቃ በኋላ በቀሪነት የሚታይ ሂሳብ መኖሩን የሚያመለክትና በታክስ በባለስልጣኑ ተቀባይነት ያገኘ ሰነድ ነው፡፡

4/ **"ማንዋል"** ማለት የመደበኛ የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመላሽ ስጋት ተኮር እንዲሆን ለማስቻል የተዘጋጀ የአሰራር ስርዓት ማለት ነው፡፡

5/**"ስጋት"** ስጋት ማለት ከመደበኛ የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመላሽ ስርዓት ጋር በተያያዘ በተቀመጠው የህግ አግባብ እንዳይከናወን እና በዚሁ ምክንያት በመንግስት ገቢ ላይ የሚፈጠሩ አሉታዊ ተፅዕኖ የሚያስከተሉ ክስተቶች ናቸው፡፡

6/ **"የስጋት ስራ አመራር"** ማለት በተጨማሪ እሴት ታክስ ተመላሽ ስርዓት የሚታዩ ስጋቶች ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ የሚለዩበት፣ የሚተነተኑበት፣ የሚስተናገዱበት እና የሚገመገሙበት የስራ አመራር ጥበብ ሲሆን በዚህም ሂደት ስጋቶች እንዲቀንሱ ወይም እንዲወገዱ የሚደረግበት የአሰራር ዘዴ ነው፡፡

7/ **"የስጋት መስፈርት"** ማለት ስጋት የመከሰት ዕድል እና የሚያስከትለውን ተፅዕኖ በማስላት የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመላሽ ጥያቄን ለማስተናገድ የተመዘገበን ሰው የስጋት ደረጃ ለመወሰን የምንጠቀምበት መስፈርት ነው፡፡

8/ **"አነስተኛ የስጋት ደረጃ "** ማለት በስጋት ምደባ መስፈርቶች መሰረት ታክስ ከፋዩ የሚገኝበት ዝቅተኛ የስጋት ደረጃ ነው፡፡

9/ **"መካከለኛ የስጋት ደረጃ"** ማለት በስጋት ምደባ መስፈርቶች መሰረት ታክስ ከፋዩ የሚገኝበት መካከለኛ የስጋት ደረጃ ነው፡፡

10/ **"ከፍተኛ የስጋት ደረጃ"** ማለት በስጋት ምደባ መስፈርቶች መሰረት ታክስ ከፋዩ የሚገኝበት ከፍተኛ የስጋት ደረጃ ነው፡፡

11/ **"ከፍተኛ ደረጃ ኦዲት"** ማለት ለመደበኛ የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመላሽ ሥርዓት የሚቀርቡ ደረሰኞች እና አስፈላጊ ተገቢ ሰነዶችን ሙሉ በሙሉ የማጣራት ሂደት ነው፡፡

12/ **"አነስተኛ ደረጃ ኦዲት"** ማለት ለመደበኛ የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመላሽ ሥርዓት ከሚቀርቡ ደረሰኞች እና አስፈላጊ ተገቢ ሰነዶች ውስጥ ስጋት

መሠረት ባደረገው የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመላሽ አሰራር ማንዋል በተቀመጠው ልክ በከፊል የማጣራት ሂደት ነው፡፡

13/ **"ታክስ ማቀናነስ"** ማለት ታክስ ከፋዩ ዕቃ ወይም አገልግሎት ሲገዛ የከፈለውን የተጨማሪ እሴት ታክስ እቃ ሲሸጥ ወይም አገልግሎት ሲቀርብ ከሚሰበስበው የተጨማሪ እሴት ታክስ ላይ በመቀነስ ተከፋይ ካለ ለታክስ ባለስልጣኑ ገቢ የሚያደርግበት ወይም በአብላጫ የተከፈለ የተጨማሪ እሴት ታክስ ካለ ወደፊት የሚሸጋገርበት ስርዓት ነው፡፡

14/ **"የካፒታል ዕቃ"** ማለት ማናቸውም ሰው ለሚያከናውነው ታክስ የሚከፈልበት የንግድ ስራ እንቅስቃሴ ጥቅም ላይ የሚውል የንግድ ስራ ሀብት ሲሆን ከአንድ ዓመት ላላነሰ ጊዜ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ያለው እና ዕቃዎችን ለማምረት ወይም አገልግሎቶችን ለመስጠት የዋለ ዕቃ ሲሆን የንግድ ዕቃዎችን አይጨምርም፡፡

15/ **"የንግድ ሥራ ሃብት"** ማለት ከአንድ ዓመት በላይ የአገልግሎት ጊዜ ያለውና ለሽያጭ የማይውል በታክስ ከፋዩ ስም የተመዘገበ ወይም የተገዛ ግዙፋዊ ህልዎት ያለው ወይም የሌለው የታክስ ከፋዩ ቋሚ ንብረት ወይም ሃብት ሲሆን ህንፃን፣ ተሽከርካሪን፣ የአገልግሎት መስጫ ወይም የንግድ መሣሪያዎችን፣ የኢንቨስትመንት ንብረቶችን፣ የድርጅት መልካም ስምና ዝናን፣ የንግድ ስምን፣ የንግድ ምልክትን እንዲሁም አዕምሯዊ ንብረቶችን ይጨምራል፡፡

16/ **"ከፍተኛ ግብይት ያለው የተመዘገበ ሰው፡-** ማለት አመታዊ ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦቱ ከአንድ መቶ ሚሊዮን ብር በላይ የሆነ ተቀናሽ የሚሆን የካፒታል ዕቃ ግዥ የፈጸመና በግዥ ላይ የከፈለው የተጨማሪ እሴት ታክስ ወደፊት ሳይሸጋገር ተመላሽ የሚፈቀድለት ማለት ነው፡፡

17/ **"ባለልዩ መብት ድርጅቶች"** ማለት ለተጨማሪ እሴት ታክስ መመዝገብ የማይገደዱ በቪየና የዲፕሎማቲክ ግንኙነት ኮንቬንሽን ለሚሲዮን ለዲፕሎማቲክ ወይም ለቆንስላ ፣ለውጭ ሀገር የዲፕሎማቲክ ወይም ለኮንስላር ሚሲዮኖች፣ በአለም አቀፍ ስምምነት መሰረት ለአለም አቀፍ ድርጅት፣ ለውጭ ሀገር መንግስት እና በሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢንቨስትመንት ማበረታቻ ደንብ ከታክሱ ነፃ እስከሆነ ድረስ ታክሱን ከፍለው በተመላሽ ስርዓት እንዲስተናገዱ የተፈቀደላቸው ናቸው፡፡

18/ **"ስራ ማስፈጸሚያ"** ማለት ለባለ ልዩ መብት ድርጅቶች የተቋቋሙበትን ተግባር ለማሳካት የሚያገለግልና ለስራ ማስፈፀሚያ የሚውል ማናቸውም ግዥ ላይ የተከፈለ ተጨማሪ እሴት ታክስ የተመላሽ ጥያቄ በድርጅቱ ኃላፊ ተፈርሞ እና ተረጋግጦ የቀረበ ማለት ነው፡፡

19/ **"የቅይጥ አቅርቦት ስሌት"** ማለት የተጨማሪ እሴት ታክስ የተከፈለበት ግብዓት ከታክስ ነፃ ለሆነ እና ታክስ ለሚከፈልበት አቅርቦት የዋለ በሚሆንበት ጊዜ ታክሱን ለመመለስ ታክስ ለማይከፈልበት ገቢ የዋለውን መጠን ለይቶ ለማስላት ጥቅም ላይ የሚውል ዘዴ ነው፡፡

20/ **"በገዥው ተይዞ የሚከፈል ታክስ"** በሀገር ውስጥ ታክስ የሚከፈልበት የዕቃና አገልግሎት ግብይት ሲከናወን ማንኛውም ወኪል ለአቅራቢው መክፈል ካለበት ታክስ ውስጥ 50% ተከፋይ ከሆነው ታክስ ላይ ተቀንሶ ለታክስ ባለስልጣኑ ገቢ የሚደረገው ቀሪውን 50% ለአገልግሎት እና ዕቃ አቅራቢው የሚከፍለው የተጨማሪ እሴት ታክስ ነው፡፡

21/ **"ወኪል"** ማለት ታክስ ከሚከፈልበት ግብይት ላይ በገዥው ተይዞ የሚከፈልን ታክስ ቀንሶ ለታክስ ባለሰልጣኑ ገቢ የሚያደርገው የመንግስት መስሪያ ቤት ወይም የመንግስት የልማት ድርጅት ወይም የግል ድርጅት ነው፡፡

22/ **"የተፋጠነ የተመላሽ ስርዓት"** ማለት በስርአቱ ተጠቃሚ እንዲሆን በኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የተመረጠ ለታክሱ የተመዘገበ ቀጥተኛ እና ቀጥተኛ ያልሆነ አምራች ላኪ ወደ ውጭ ለሚልከው ምርት ግብዓት ከሀገር ውስጥ ሲገዛ የከፈለው ታክስ ምርቱ ወደ ውጭ ከመላኩ በፊትም ቢሆን ተመላሽ የሚደረግበት ስርዓት ነዉ፡፡

23/ **"አዋጅ"** ማለት የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 1341/2016 ነው፡፡

24/ **"ታክስ"** ማለት ተጨማሪ እሴት ታክስ ነው፡፡

25/ በዚህ መመሪያ በወንድ ጾታ የተገለፀው ለሴት ጾታም ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

26/ በዚህ መመሪያ ውስጥ ትርጉም ያልተሰጣቸው ቃላት በሌሎች የታክስና ተዛማጅ ህጎች የተሰጣቸውን ትርጉም ይይዛሉ፡፡

3. <u>የተፈጻሚነት ወሰን</u>

ይህ መመሪያ የተከፈለ የተጨማሪ እሴት ታክሰ ተመላሽ በሚደረግለት ሰው ላይ ተፈጻሚ ይሆናል።

ክፍል ሁለት

የተጨማሪ እሴት ታክስ የማቀናነስ እና የተመላሽ ስርዓት

4. በዜሮ የማስከፈያ ልክ እና በመደበኛ 15 በመቶ የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመላሽ የሚፈቀድባቸው ግብይቶች

1. የተመዘገበ ሰው በአንድ የሂሳብ ጊዜ ታክስ የሚከፈልበት ግብይት ዋጋ ውስጥ ቢያንስ 50 በመቶ በዜሮ የማስከፈያ ልክ ተፈፃሚ በሆነ ታክስ በተከፈለበት ግብይት ላይ በብልጫ የተከፈለ ታክስ ተመላሽ ጥያቄው በቀረበ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ተመላሽ የሚደረገው ለሚከተሉት ግብይቶች ነው፡-

   ሀ) ለውጭ ገበያ የሚቀርቡ አቅርቦቶች፣

   ለ) ከኢትዮጵያ ውጭ በሚጓዝ አውሮፕላን ተሽከርካሪ ወይም ባቡር ላይ የተጫኑ ከኢትዮጵያ ውጭ ለጥቅም ወይም ለፍጆታ የሚውሉ የጉዞ ዕቃዎች፤

   ሐ) ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የሚቀርብ ወርቅ፤

2. የተጨማሪ እሴት ታክስ ቀንሰው በሚያስቀሩ አካላት ወይም በገዥው ተይዞ የተከፈለ የተጨማሪ እሴት ታክስ ታክስ ከፋዩ ታክስ የሚከፈልበትን ግብይት በሚያከናውንበት ጊዜ በተቀበለው ደረሰኝ የተመለከተውን ገንዘብ መጠን ለሁለት ወራት በግብይት ላይ ከተከፈለ ታክስ ወይም ተከፋይ ከሚሆነው ታክስ ጋር እንዲካካስ አድርጎ በደረሰኙ ላይ የተመለከተውን የገንዘብ መጠን በግብይት ላይ ከተከፈለው ወይም ተከፋይ ከሚሆነው ታክስ የበለጠ ሆኖ ከተገኘ ጥያቄው በቀረበ በ45 ቀናት ውስጥ ተመላሽ ይደረጋል፡፡
3. ታክስ ከፋዩ ለተጨማሪ እሴት ታክስ ከተመዘገበበት ቀን በፊት ባሉት የስድስት ወር ጊዜ ውስጥ ለንግድ ዕቃዎች እና ከተመዘገበበት ቀን በፊት ባሉት የሶስት ዓመት ጊዜ ውስጥ በካፒታል ዕቃዎች ላይ የተከፈለ ተጨማሪ እሴት ታክስ እንዲቀናነስ የተፈቀደ እንደሆነ በሂሳብ ጊዜው በግብዓት ላይ የተከፈለው ታክስ በግብይት ወይም ሽያጭ አቅርቦት ላይ ከተከፈለው ወይም ከተሰበሰበው ላይ እንዲቀናነስ ተደርጎ ቀሪው ሂሳብ ካለ የተመላሽ ጥያቄው በቀረበ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ተመላሽ ይደረጋል፡፡
4. አንድ ለተጨማሪ እሴት ታክስ የተመዘገበ ሰው የንግድ ስራውን በማስፋፋት ሂደት ግንባታው ባልተጠናቀቀ ህንፃ ላይ የተከፈለው የተጨማሪ እሴት ታክስ፤ህንፃው

ተጠናቆ ታክስ ለሚከፈልበት የንግድ ተግባር መዋሉ ሲረጋገጥ በግብዓቱ ላይ የተከፈለው ታክስ በግብይት ላይ ከተከፈለው ታክስ ላይ በሂሳብ ጊዜው ውስጥ እንዲቀናነስ ተደርጎ ቀሪ ሂሳብ ካለ የተመላሽ ጥያቄው በቀረበ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ተመላሽ ይደረጋል፡፡

5. ከፍተኛ ግብይት ያለው ወይም ዓመታዊ ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦቱ ከአንድ መቶ ሚሊዮን ብር በላይ የሆነ የተመዘገበ ሰው ተቀናሽ እንዲደረግ የተፈቀደ የካፒታል ዕቃ ግዥ ላይ የተከፈለ የተጨማሪ እሴት ታክስ እንዲመለስለት ጥያቄ ያቀረበ እንደሆነ ጥያቄውን ባቀረበ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ተመላሽ ይደረግለታል፡፡
6. ለታክሱ በተመዘገበ ሰው በከፊል ታክስ ለሚከፈልበት እና በከፊል ከታክስ ነፃ ለሆነ ግብይት በዋለ ዕቃና አገልግሎት ግዥ ላይ የተከፈለ የተጨማሪ እሴት ታክስ በሂሳብ ጊዜው ውስጥ ያከናወነው ታክስ የሚከፈልበት ግብይት ዋጋ ለጠቅላላ ግብይት ዋጋ ሲካፈል፡-

   ሀ/ ውጤቱ 0.95 (ዜሮ ነጥብ ዘጠኝ አምስት) ወይም ከዚያ በላይ ከሆነ ተቀናሽ የሚደረግ ግዥ ላይ በግብዓቱ ላይ የተከፈለውን ታክስ ሙሉ በሙሉ በማቀናነስና በአዋጁ መሰረት ለወደፊት በማሸጋገር ቀሪ ሂሳብ መኖሩ ሲረጋገጥ ተመላሽ ይደረጋል፡፡

   ለ/ ውጤቱ 0.05 (ዜሮ ነጥብ ዜሮ አምስት) ወይም ከዚያ በላይ ከሆነ እና ከ0.95 (ዜሮ ነጥብ ዘጠኝ አምስት) በታች ከሆነ ታክስ ለሚከፈልበት በዋለው ልክ በማቀናነስ እና በአዋጁ መሰረት ለወደፊት በማሸጋገር ቀሪ ሂሳብ መኖሩ ሲረጋገጥ ተመላሽ ይደረጋል፡፡

   ሐ/ ውጤቱ ከ0.05 (ዜሮ ነጥብ ዜሮ አምስት) በታች ከሆነ በግዥው ላይ የተከፈለው ተጨማሪ እሴት ታክስ ሙሉ በሙሉ ተቀናሽ ወይም ተመላሽ አይደረግም፡፡

5/ <u>ወደፊት ሳይሸጋገር ተመላሽ የሚደረግ በብልጫ የተከፈለ የግብዓት ታክስ</u>

1. የተመዘገበ ሰው በአንድ የሂሳብ ጊዜ ካከናወነው አቅርቦት ዋጋ ውስጥ 50 በመቶ ወይም ከዚያ በላይ ዜሮ የማስከፈያ ልክ ተፈፃሚ የሚደረግበት ከሆነ፤ የተመዘገበው ሰው በሂሳብ ጊዜው ወይም የተጨማሪ እሴት ታክስ ካስታወቀበት ጊዜ ጀምሮ በሚቆጠር በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ጥያቄውን ማቅረብ አለበት፡፡

2. በውጭ ንግድ ማበረታቻ አዋጅ ቁጥር 768/2004 (እንደተሻሻለ) አንቀፅ 5 በተደነገገው መሰረት በተፋጠነ የተመላሽ ስርዓት እንዲስተናገድ የተፈቀደለት ላኪ፣ ምርቱን ወደ ውጭ ከመላኩ በፊት ወይም ምርቱን ወደ ወጭ መላክ ሳይጠበቅበት በሀገር ውስጥ ባከናወነው የግብዓት ግዥ ላይ የከፈለውን ተጨማሪ እሴት ታክስ በየወሩ ለባለስልጣኑ ጥያቄውን ማቅረብ የሚችል ሲሆን ጥያቄው በቀረበ በሰባት ቀናት ጊዜ ውስጥ ተመላሽ ይደረጋል፡፡

ክፍል ሶስት

የመደበኛ የተመላሽ ስርዓት አፈፃፀም

6/ መደበኛ የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመላሽ ስርዓት

1. በታክስ ባለስልጣኑ የሚሰጥ መደበኛ የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመላሽ አገልግሎት እና የሚከናወን የማጣራት ስርዓት በሚመለከት በመረጃ በተደገፈ የስጋት መምረጫ መስፈርት መሰረት የታክስ ከፋዩን የስጋት ደረጃ በመለየት እና የፋይል ስምሪት ማኑዋልን መሰረት በማድረግ በሚመለከተው የታክስ ኦዲት ወይም አገልግሎት ኦዲት የተመላሽ ጥያቄውን የማጣራትና የመወሰን ስራ የሚከናወን ይሆናል፡-
2. የታክስ ተመላሽ አገልግሎት የሚጠይቅ ታክስ ከፋይ የተመዘገበው በግብር ዘመኑ በመሆኑ ምክንያት መረጃ ማግኘት እና የስጋት ደረጃ ማውጣት ባልተቻለ ጊዜ :-

   ሀ/ ለአቅራቢው በባንክ በኩል ክፍያ የፈጸመበትን ማስረጃ ካቀረበ፣ ወይም

   ለ/ ተጨማሪ እሴት ታክስ ቀንሶ የሚያስቀረው ሰው ክፍያው የተፈፀመለት በባንክ በኩል መሆኑን የሚያስረዳ ማስረጃ ካቀረበ የተመላሽ ጥያቄው በአነስተኛ ደረጃ ኦዲት ተጣርቶ ተመላሽ ይደረጋል፡፡

3. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 2 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ለግብይቱ ክፍያ የተፈፀመው በባንክ በኩል ካልሆነ ታክስ ከፋዩ የሚያቀርበው የታክስ ተመላሽ ጥያቄ በከፍተኛ ደረጃ ኦዲት ታጣርቶ ተመላሽ ይደረጋል፡፡
4. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1፣ 2 እና 3 የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ ፡-

ሀ/ በአነስተኛ የስጋት ደረጃ የሚመደብ እና ኦዲት ሳይደረግ ተመላሽ የሚደረግለት ታክስ ከፋይ የተመላሽ ጥያቄ ባቀረበ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ በማኑዋል መሰረት ማጣራት ተደርጎ ተመላሽ ይደረግለታል፡፡

ለ/ በአነስተኛ የስጋት ደረጃ የሚመደብ እና ኦዲት ከተደረገ በኋላ ተመላሽ የሚፈፀምለት ታክስ ከፋይ የተመላሽ ጥያቄውን ባቀረበ በአርባ አምስት ቀን ጊዜ ውስጥ ተመላሽ ይደረግለታል፡፡

7/ በህግ ከተጨማሪ እሴት ታክስ ነፃ በተደረገ ሰው ላይ የሚፈፀም የታክስ ተመላሽ ስርዓት

1. በአዋጁ የተጨማሪ እሴት ታክስ ነፃ መብት ያለው ሆኖ በተመላሽ ስርዓት እንዲስተናገድ የተፈቀደለት ሰው በአገር ውስጥ ታክሱ የሚከፈልበት ግብይት ሲያከናውን ታክሱን ከፍሎ በተመላሽ ስርዓት እንዲስተናገድ ይደረጋል፡፡
2. የታክስ ነፃ ባለመብቱ ለአቅራቢው ክፍያ የፈፀመው በባንክ በኩል መሆኑን የሚያስረዳ ማስረጃ ካቀረበ የተመላሽ ጥያቄው በቀረበ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ተመላሽ ይደረግለታል፡፡
3. የታክስ ነፃ ባለመብቱ ለአቅራቢው ክፍያ የፈፀመው በባንክ በኩል ካልሆነ የተመላሽ ጥያቄው በቀረበ በአርባ አምስት ቀናት ጊዜ ውስጥ ተመላሽ ይደረጋል፡፡

8/ በተለያዩ የስራ ክፍሎች የሚወጡ የተመላሽ ውሳኔዎች

በታክስ ኦዲት፣በኢንቨስትጌሽን ኦዲት፣ በአገልግሎት ኦዲት እና በሌሎች የስራ ክፍሎች የሚወጡ የተመላሽ ውሳኔዎች የተመላሽ ጥያቄን በተመለከተ ታክስ ከፋዩ ውሳኔው ከደረሰው ቀን ጀምሮ በሚቆጠር 6 ወር ጊዜ ውስጥ የተመላሽ ጥያቄውን ማቅረብ የሚችል ሲሆን በድጋሚ ሰነድ ማቅረብ ሳያስፈልግ መለስተኛ ማጣራት በማድረግ ጥያቄው በቀረበ በ45 ቀን ጊዜ ውስጥ ተመላሽ ይደረግለታል፡፡

ክፍል አራት

የታክስ ተመላሽ ጥያቄ የሚያቀርብ ሰው ማሟላት ያለበት ቅድመ ሁኔታ

9/ በዜሮ የማስከፈያ ልክ የተጨማሪ እሴት ታክስ የሚከፈልባቸው ግብይቶች ላይ ታክስ ከፋዮች የተመላሽ መጠየቂያ ቅፅ ስለመሙላት እና ማስረጃ ስለማቅረብ

1. ታክስ ተመላሽ እንዲደረግለት የሚጠይቅ ማንኛውም ሰው የተመላሽ ጥያቄውን በሚያቀርብበት ጊዜ በዚህ መመሪያ የተመለከተውን ቅድመ ሁኔታ በማሟላት

ጥያቄውን የታክስ ባለስልጣኑ ባዘጋጀው የተመላሽ መጠየቂያ ቅፅ ሞልቶ ማቅረብ አለበት፡፡

2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ ታክስ ከፋዩ የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመላሽ እንዲደረግለት ሲጠይቅ የሚከተሉትን ማስረጃዎችን በአንድነት አሟልቶ በሚከተለው አግባብ ከተሞላው ቅፅ ጋር አያይዞ ማቅረብ አለበት፡፡

ሀ/ በአንድ የሂሳብ ጊዜ ውስጥ ከተከናወነው ግብይት መካከል 50 በመቶ ወይም ከዚያ በላይ የሚሆነውን ግብይት ዕቃን ወደ ውጭ ለመላክ በግብዓትነት የሚውል ግዥ ላይ የተከፈለ የተጨማሪ እሴት ታክስ መሆኑን፣ ወደ ውጭ የተላከውን ዕቃ መጠን እና ዕቃው ለውጭ ገበያ የተላከ መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ፣

ለ/ ወደ ውጭ የሚላኩ ዕቃዎች በተጠቀሰው የሂሳብ ጊዜ ከተከናወኑ ግብይቶች ዋጋ ሃምሳ በመቶ (50%) ያላቸው መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ፣

ሐ/ ምርቱ ወይም እቃው ለውጪ ገበያ መላኩን የሚያሳይ የጉምሩክ ዲክላራሲዮን፣

መ/ ምርቱ ወይም እቃው ለውጪ ገበያ መላኩን የሚያሳይ የማስጫኛ ወይም /ለትራንስፖርት/ ክፍያ የተፈፀመበት ሰነድ፣

ሠ/ የባንክ ፈቃድ ደረሰኝ፣

ረ/ ሽያጩ የውጪ ምንዛሬ ያስገኘ መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ፣

ሰ/ በግብዓት ላይ የተከፈለ የተጨማሪ እሴት ታክስ ህጋዊ ኦርጅናል ደረሰኝ እና ታክስ ደቢት ሰነድ፣ ክሬዲት ሰነድ፣ ሪቨርስ ታክስ የተከፈለበት ማስረጃ፣

ሸ/ ወደ ውጭ ለተላኩት ዕቃዎች ግብዓት የተከፈለውን የተጨማሪ እሴት ታክስ ድርሻና ስሌት የሚያመለክት በሚመለከተው አካል የተጠና የግብዓት ምርት ጥምርታ ወይም በድርጅቱ የተጠና በባለስልጣኑ ተቀባይነት ያላቸው ማስረጃዎች፣

ቀ/ ዕቃው ለተላከለት ገዥ የተደረገውን የዕቃ ሽያጭ ውል ተያይዞ መቅረብ አለበት፡፡

3. ለውጭ ሀገር የሚቀርቡ አገልግሎቶች የተመላሽ ጥያቄ በሚያቀርቡበት ጊዜ ማሟላት ያለባቸው ማስረጃዎች፡-

ሀ) ከተከናወኑ የአገልግሎቶች የአቅርቦት ዋጋ ሃምሳ በመቶ (50%) በዜሮ የማስከፈያ ልክ ያላቸው መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ፣

ለ) በተጠቀሰው የሂሳብ ጊዜ አገልግሎቱን ከተቀበለው (ከገዥው) ጋር የተገባው የውል ስምምነት ሰነድ፣

ሐ) የውጪ ምንዛሪ የተገኘበት የባንክ ሰነድ የሚያመለክቱና በባለስልጣኑ ተቀባይነት ያላቸው ማስረጃዎች፣

መ) በግብዓት ላይ የተከፈለ የተጨማሪ እሴት ታክስ ህጋዊ ኦርጅናል ደረሰኝ፣ ታክስ ደቢት ሰነድ፣ ክሬዲት ሰነድ፣ ሪቨርስ ታክስ የተከፈለበት ማስረጃ ማቅረብ አለባቸው፡፡

4. በዓለም አቀፍ የትራንስፖርት አገልግሎት የተሰማሩ የተመላሽ ጥያቄ በሚያቀርቡበት ጊዜ ማሟላት ያለባቸው ማስረጃዎች፡-

ሀ) ከዚህ አገልግሎት ጋር በቀጥታ ለተገናኙ አገልግሎቶች የተከፈለበት ማስረጃ ማቅረብ፣ወይም

ለ) አገልግሎቱ በሚሰጥበት ወቅት ለፍጆታ ለሚውሉ የቅባት ዘይቶችና ሌሎች ለላቂ የቴክኒክ ዕቃዎች ግብይቶች በግብዓት ላይ የተከፈለ በባለስልጣኑ ተቀባይነት ያላቸው የተጨማሪ እሴት ታክስ ኦርጅናል ህጋዊ ደረሰኝ፣ ታክስ ዴቢት ሰነድ፣ ክሬዲት ሰነድ፣ሪቨርስ ታክስ የተከፈለበት ማስረጃ ማቅረብ አለባቸው፡፡

5. ለብሔራዊ ባንክ የሚቀርቡ የአገር ውስጥ ወርቅ አቅራቢዎች የተመላሽ ጥያቄ በሚያቀርቡበት ጊዜ ማሟላት ያለባቸው ማስረጃዎች፡-

ሀ) ከብሔራዊ ባንኩ የተሰጣቸው ማስረጃ፣

ለ) ወርቁን ለማቅረብ በአገር ውስጥ የግብዓት ግዥ ላይ የተከፈለ የተጨማሪ እሴት ታክስ ያላቸው መሆኑን የሚያሳይ ህጋዊ ኦርጅናል ደረሰኝ ታክስ

ዴቢት ሰነድ፣ ክሬዲት ሰነድ፣ ሪቨርስ ታክስ የተከፈለበት ማስረጃ እና ሌሎች ማስረጃዎች አያይዘው ማቅረብ አለባቸው፡፡

10/ በተፋጠነ የተመላሽ ስርዓት ተጠቃሚ ለሚቀርብ የተመላሽ ጥያቄ መጠየቂያ ቅፅ ስለመሙላት እና ማስረጃ ስለማቅረብ

1. የተጨማሪ እሴት ታክሰ ተመላሽ እንዲደረግለት የሚጠይቅ የተፋጠነ ተመላሽ ስርዓት ተጠቃሚ የተመላሽ ጥያቄውን በሚያቀርብበት ጊዜ በዚህ መመሪያ የተመለከተውን ቅድመ ሁኔታ በማሟላት ጥያቄውን የታክስ ባለስልጣኑ ባዘጋጀው የተመላሽ መጠየቂያ ቅፅ ሞልቶ ማቅረብ አለበት፡፡
2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ በተፋጠነ የተመላሽ ስርዓት ተጠቃሚ እንዲሆን የተመረጠ ለታክሱ የተመዘገበ ታክስ ከፋይ ምርቱን ወደ ውጭ ከመላኩ በፊት በአገር ውስጥ የግብዓት ግዥ ላይ የከፈለው ታክስ ተመላሽ ይደረግለታል፡፡ ለዚህ ንዑስ አንቀፅ አፈፃፀም፡-

   ሀ) ታክስ ከፋዩ በተፋጠነ ታክስ ተመላሽ ስርዓት እንዲስተናገድ የተፈቀደበትን ከኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የተሰጠውን ማስረጃ ማቅረብ አለበት፡፡

   ለ) በአገር ውስጥ የግብዓት ግዥ ላይ የተጨማሪ እሴት ታክስ የተከፈለበትን ህጋዊ ኦርጅናል ደረሰኝ ታክስ ዴቢት ሰነድ፣ ክሬዲት ሰነድ፣ ሪቨርስ ታክስ የተከፈለበት ማስረጃ ማቅረብ አለበት፡፡

3. ታክስ ከፋዩ ቀደም ሲል በ 7 ቀናት ውስጥ ተመልሶ የነበረው ተመላሽ ምርቱ ወደ ውጭ ከተላከ በኋላ ምርቱ ወደ ውጭ መላኩን የሚያሳይ ከንግድ ስራው እንቅስቃሴ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ሙሉ ሰነዶች ወይም መረጃዎች ቀርበው ቢያንስ በአመት አንድ ጊዜ ኦዲት መደረግ ያለበት ሲሆን በሚደረስበትም ውጤትም ቀደም ሲል ያልተገባ ተመላሽ ወስዶ ከሆነ እንዲመለስ ይደረጋል፡፡ ለዚህም አፈፃፀም:-

   ሀ) ምርቱ ወይም እቃው ለውጪ ገበያ መላኩን የሚያሳይ የጉምሩክ ዲክላራሲዮን፤

   ለ) ምርቱ ወይም እቃው ለውጪ ገበያ መላኩን የሚያሳይ የማስጫኛ ወይም /ለትራንስፖርት/ ክፍያ የተፈፀመበት ሰነድ፤

   ሐ) የባንክ ፈቃድ ደረሰኝ ፤

መ) ሸያጩ የውጪ ምንዛሬ ያስገኘ መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ የቀረበላቸው መሆኑን፤

ሠ) በግብዓት ላይ የተከፈለ የተጨማሪ እሴት ታክስ ህጋዊ ኦርጅናል ደረሰኝ ታክስ ዴቢት ሰነድ፣ ክሬዲት ሰነድ፣ ሪቨርስ ታክስ የተከፈለበት ማስረጃ ማቅረብ አለባቸው፡፡

ረ) ወደ ውጭ ለተላኩት ዕቃዎች ግብዓት የተከፈለውን የተጨማሪ እሴት ታክስ ድርሻና ስሌት የሚያመለክት በሚመለከተው አካል የተጠና የግብዓት ምርት ጥምርታ ወይም በድርጅቱ የተጠና በባለስልጣኑ ተቀባይነት ያላቸው ማስረጃዎች፤

ሰ) ዕቃው ለተላከለት ገዥ የተደረገውን የዕቃ ሽያጭ ውል ተያይዞ መቅረብ አለበት፡፡

11/ በመደበኛ 15 በመቶ የማስከፈያ ልክ የተጨማሪ እሴት ታክስ የሚከፈልባቸው ግብይቶች ላይ የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመላሽ የሚጠይቁ ታክስ ከፋዮች

1. በመደበኛ 15 በመቶ የማስከፈያ ልክ የተጨማሪ እሴት ታክሰ ተመላሽ እንዲደረግለት የሚጠይቅ ታክስ ከፋይ የተመላሽ ጥያቄውን በሚያቀርብበት ጊዜ ከተሞላው የተመላሽ መጠየቂያ ቅፅ ጋር የሚከተሉትን ማስረጃዎች ማቅረብ አለባቸው፡፡

   ሀ) ታክስ የተከፈለበት ግብዓት በምርት ሂደት ጥቅም ላይ መሆኑን የሚያስረዳ በሚመለከተው አካል የተጠና የምርት ጥምርታ ማስረጃ ፤ ወይም በድርጅቱ የተጠና በባለስልጣኑ ተቀባይነት ያላቸው ማስረጃዎች፤

   ለ) የተሸጠ ምርት ወይም ዕቃ እና ያልተሸጠ ወይም በመጋዘን የሚገኝ የስቶክ ማረጋገጫ ማስረጃ፤

   ሐ) በግብዓት ግዥው ላይ ታክሱ የተከፈለበት ህጋዊ ኦርጅናል ደረሰኝ ታክስ ዴቢት ሰነድ፣ ክሬዲት ሰነድ፣ ሪቨርስ ታክስ የተከፈለበት ማስረጃ እና ተያያዥ ማስረጃዎች፤

2. በገዢው ተይዞ የሚከፈል ተጨማሪ እሴት ታክስን በተመለከተ በሂሳብ ጊዜው ውስጥ ከወኪሎች ጋር የተደረገውን የግብይት መጠን የሚያሳይ ማስረጃ መቅረብ አለበት፡፡ ለዚህ አፈፃፀም፡-

ሀ) ታክስ ከፋዩ ታክስ የሚከፈልበትን ግብይት በሚያከናውንበት ጊዜ በተቀበለው ደረሰኝ የተመለከተውን ገንዘብ መጠን ለሁለት ወራት በግብይት ላይ ከተከፈለ ታክስ ወይም ተከፋይ ከሚሆነው ታክስ ጋር እንዲካካስ ወይም እንዲቀናነስ አድርጎ በደረሰኙ ላይ የተመለከተውን የገንዘብ መጠን በግብዓት ላይ ከተከፈለው ወይም ተከፋይ ከሚሆነው ታክስ የበለጠ ሆኖ ከተገኘ የተመላሽ ጥያቄው ማቅረብ አለበት፡፡

ለ) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 2(ሀ) የተደነገገው ቢኖርም ታክስ ከፋዩ 50% በላይ የሚሆነውን ግብይት ያከናወነው ከወኪሎች ጋር ከሆነ በደረሰኙ የተመለከተውን የገንዘብ መጠን በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ በግብዓት ላይ ከተከፈለ ታክስ ወይም ተከፋይ ከሚሆነው ታክስ ጋር እንዲካካስ አድርጎ በብልጫ የሚታየውን ገንዘብ የተመላሽ ጥያቄ ማቅረብ ይችላል፡፡

ሐ) የተመላሽ ጥያቄው ሲቀርብ የተጨማሪ እሴት ታክስ ተቀንሶ የተያዘበት በገዢው ተይዞ የሚከፈል ተጨማሪ እሴት ታክስ ህጋዊ ኦርጅናል ደረሰኝ እና የተጨማሪ እሴት ታክስ የተከፈለበት ህጋዊ ኦርጅናል ደረሰኝ፣ ታክስ ዴቢት ሰነድ፣ ክሬዲት ሰነድ፣ ሪቨርስ ታክስ የተከፈለበት ማስረጃ ሲያቀርብ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ጥያቄው ተጣርቶ ገንዘቡ መመለስ አለበት፡፡

3. የተመዘገበ ሰው በአዲስ ህንጻ ግንባታ ወይም በማስፋፊያ ግንባታ ጊዜ የተከፈለ ተጨማሪ እሴት ታክስ ተመላሽ እንዲደረግ የሚጠይቅ ታክስ ከፋይ፡-

ሀ) ለአዲስ ህንጻ ግንባታ ወይም ማስፋፊያ በዋለ ዕቃ ወይም አገልግሎት ግዥ ላይ ተጨማሪ እሴት ታክስ የተከፈለበትን ህጋዊ ኦርጂናል ደረሰኝ ታክስ ዴቢት ሰነድ፣ ክሬዲት ሰነድ፣ ሪቨርስ ታክስ የተከፈለበት ማስረጃ ማቅረብ አለበት፡፡

ለ) ህንጻው የተሰራው በህንጻ ተቋራጭ ከሆነ የህንጻ ተቋራጩ በሚያቀርበው የግብዓት ዋጋ ዝርዝር መሠረት የተከፈለውን ተጨማሪ እሴት ታክስ መጠን የሚያሳይ ደረሰኝ ማቅረብ አለበት፡፡

ሐ) ህንጻው የተጠናቀቀ እና ስራ መጀመር የሚችል መሆኑን የሚያረጋግጥ ስልጣን ከተሰጠው የመንግስት ተቋም የተሰጠ ማስረጃ ማቅረብ አለበት፡፡

4. ለእያንዳንዱ የተመላሽ ዓይነት በመጠየቂያ ቅፁ የሚቀርበው የታክስ ተመላሽ ጥያቄ እያንዳንዱ ግብይት በዝርዝር እና የተጠቃለለ ሆኖ ታክስ በተከፈለበት ማስረጃ የተደገፈ መሆን ይኖርበታል፡፡
5. ታክስ ከፋዩ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 4 በተገለፀው መሰረት ማመልከቻ ያቀረበ እንደሆነ እና የታክሱ ባለስልጣን የቀረበው ጥያቄ ተገቢ መሆን አለመሆኑን በአገልግሎት ታክስ ኦዲት ተጣርቶ የተመላሽ ጥያቄ ማመልከቻው በቀረበለት በ45 ቀናት ውስጥ ተመላሹን ገንዘብ መክፈል አለበት፡፡
6. የተጨማሪ እሴት ታክስ ምዝገባ የተሰረዘበት ታክስ ከፋይ የሚያቀርበው የተመላሽ ጥያቄ ታክስ ከፋዩ ለተመዘገበበት የመጨረሻ የሂሳብ ጊዜ የሂሳብ ማስታወቂያ ማቅረብ በሚገባው በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ወይም ታክስ ከፋዩ በአንድ ወር ጊዜ ለማቅረብ የማይችልበት አስገዳጅ ሁኔታ መኖሩ በማስረጃ የተረጋገጠ እንደሆነ በ6 (ስድስት) ወር ጊዜ ጥያቄውን ለታክሱ ባለስልጣን ማቅረብ አለበት፡፡

12/ <u>በባለ ልዩ መብት ተጠቃሚ ድርጅት የሚቀርብ የተመላሽ ጥያቄ፤</u>

1. የተጨማሪ እሴት ታክሰ ተመላሽ እንዲደረግለት የሚጠይቅ በባለ ልዩ መብት ተጠቃሚ ድርጅት የታክስ ተመላሽ እንዲደረግለት ሲጠይቅ የተመላሽ መጠየቂያ ቅፅ ጋር የሚከተሉትን ማስረጃዎች ለታክስ ባለስልጣኑ ማቅረብ አለበት፦

ሀ) የእያንዳንዱ ግብይት በዝርዝር እና የተጠቃለለ ታክስ የተከፈለበትን ማስረጃ፣

ለ) ለተመላሽ የሚቀርቡ ሰነዶችን የሚያረጋግጠው ሰው የፊርማ ናሙና በቅድሚያ በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የፕሮቶኮል ዋና ዳይሬክተር (የስራ ሀላፊ) የታወቀና የተረጋገጠ ማስረጃ፣

ሐ) የባለልዩ መብት ድርጅቶች በሚያከናውኑት ማናቸውም ዕቃ ወይም አገልግሎት ግዥ ላይ የተከፈለ የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመላሽ ጥያቄ በታክስ ተመላሽ መጠየቂያ ቅፅ ተሞልቶ ሲቀርብ ለተቋሙ ስራ

ማስፈፀሚያ የዋለ መሆኑን የሚያረጋግጥ ኃላፊነት በተሰጠው ሃላፊ ወይም የስልጣን ውክልና ባለው የስራ ሀላፊ በፊርማ የተረጋገጠ ማስረጃ፣

መ) የተመላሽ ጥያቄ የቀረበበት የተጨማሪ እሴት ታክስ የተከፈለበት ህጋዊ ኦርጂናል የታክስ ደረሰኝ፣ ታክስ ዴቢት ሰነድ፣ ክሬዲት ሰነድ በታክስ ህጉ ድንጋጌ መሰረት የተሟላ፣ የተዘጋጀበትንና የተሰጠበትን ትክክለኛ ቀን የሚያመለክት ማስረጃ፣

ሠ) ባለ ልዩ መብቱ ክፍያ የፈፀመው በባንክ ከሆነ ክፍያው የተፈፀመበትን የአቅራቢውን የባንክ አካውንት ወይም የባንክ አድቫይስ ወይም አቅራቢው ክፍያው የተፈጸመለት ስለመሆኑ የሚያረጋግጥ ህጋዊና ኦርጅናል ደረሰኝ፣

2. የታክስ ተመላሽ ጥያቄው የባለልዩ መብት ድርጅቱ ከሚያከናውነው ግንባታ ስራ ጋር የተያያዘ ከሆነ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ 1 የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ፡-

ሀ) ከስራ ተቋራጩ ጋር የተፈራረመበትን ህጋዊ የሆነ የግንባታ ስራ ውል፣

ለ) የባለልዩ መብት ድርጅቱ ለስራ ተቋራጩ የታክስ ክፍያ ከፈፀመበት ሰነድ ጋር ተያይዞ መቅረብ አለበት፡፡

3. በአንድ ነጠላ የተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ የተከፈለው የተጨማሪ እሴት ታክስ ልክ ብር 100 በታች ከሆነ ታክሱ ተመላሽ አይደረግም፡፡

4. ባለልዩ መብት ድርጅቶች የሚያቀርቡት የተመላሽ ጥያቄ ለስራቸው ማስፈፀሚያ እንዲውል በኢትዮጵያ ውስጥ ባከናወኑት የዕቃና አገልግሎት ግዥ ላይ የተከፈለ የተጨማሪ እሴት ታክስ ብቻ ነው፡፡

5. በባለልዩ መብት ድርጅቶች የሚቀርብ የተመላሽ ጥያቄ አቅርቦቱ ከተከናወነበት በደረሰኙ ላይ ከተመለከተው ቀን ጀምሮ በሚቆጠር በአንድ ወር ጊዜ ወይም ለታክስ ባለስልጣኑ በሚያቀርበው አሳማኝና አግባብነት ያለው ማስረጃ መሰረት በ6 ወር ጊዜ ውስጥ ማቅረብ ያለበት ሲሆን በተጠቀሰው ጊዜ ባይቀርብ የተመላሽ ጥያቄው ተቀባይነት አይኖረውም፡፡

ክፍል አምስት

የተመላሽ አፈፃፀም ስርዓት

13. ስለታክስ ተመላሽ ጥያቄ ማጣራትና የክፍያ አፈጻፀም፤

1. ማንኛውም ታክስ ከፋይ የንግድ ፈቃዱ ከተሰረዘ በኃላ በሚያከናውነው ግዥ ላይ ለከፈለው ተጨማሪ እሴት ታክስ የተመላሽ ጥያቄ ማቅረብ አይቻልም፡፡
2. ለህንፃ ግንባታ በሚውል ግብዓት ግዥ ላይ የተከፈለ ተጨማሪ እሴት ታክስ ተመላሽ የሚጠይቀው የህንፃው ግንባታ ተጠናቆ ገቢ ማመንጨት በተጀመረበት የመጀመሪያው የሂሳብ ጊዜ ከሰበሰበው ታክስ ላይ እንዲቀናነስ ከተደረገ በኋላ ቀሪ ሂሳብ ካለው ቀጥሎ ባለው ወር ውስጥ ጥያቄውን ማቅረብ ይችላል፡፡
3. በዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀፅ (2) የተደነገገው ቢኖርም ለህንፃው ግንባታ በዋለ ግብዓት ላይ የተከፈለ ተጨማሪ እሴት ታክስ ግንባታው ተጠናቆ ታክስ የሚከፈልበት ገቢ ማመንጨት ከመጀመሩ በፊት በተደረጉ ሌሎች ታክስ የሚከፈልባቸው ግብይቶች ላይ ከተሰበሰበ ታክስ ጋር ሊቀናነስ አይችልም፡፡
4. ማንኛውም የተመዘገበ ታክስ ከፋይ በግብዓት ላይ የከፈለው ታክስ የካፒታሉ አካል ሆኖ ከተመዘገበ እና የእርጅና ቅናሽ ወጪ እንዲታሰብለት ከተደረገ ታክሱ ተመላሽ አይደረግም፡፡
5. በማንኛውም ሁኔታ የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመላሽ ጥያቄ ሲቀርብ የተጨማሪ እሴት ታክሱን ደረሰኝ የሰጡ አቅራቢዎች በትክክል ለታክሱ የተመዘገቡና በሽያጫቸው ላይ የተሰበሰበውን ታክስ በጊዜው አሳውቀው በመክፈል ላይ የሚገኙ መሆኑን በገንዘብ ሚኒስቴር የወጣው የታክስ ኦዲት የሚከናወንበትን ስርዓትና የታክስ ስሌት ማስታወቂያ የሚወጣበትን አኳኋን ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 1063/2017 አንቀፅ 13 ንዑስ አንቀፅ 5 (ሀ) እና (ለ) በተገለጸው አግባብ የማጣራት ስራው ተግባራዊ ይደረጋል፡፡
6. ለታክስ ከፋዩ የተወሰነለት የተመላሽ ሂሳብ በቅድሚያ በፌደራል ታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀፅ 50 ንዑስ አንቀፅ 4 በተገለፀው መሰረት እንዲስተናገድ ይደረጋል፡፡
7. የተመዘገበው ሰው ተመላሽ ሊከፈለው በሚገባ በማናቸውም የሂሳብ ጊዜ የተጨማሪ እሴት ታክስ የማስታወቅ ግዴታውን ያልተወጣ ሆኖ ከተገኘ የታክሱ ባለስልጣን የተመዘገበው ሰው የተጨማሪ እሴት ታክስ ሳያስታውቅ ለቆየበት የሂሳብ ጊዜ ሁሉ

የማስታወቅ ግዴታውን እስከሚወጣ ድረስ ተመላሽ ገንዘብ ሳይከፈለው እንዲቆይ ሊያደርግ ይችላል፡፡

8. የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመላሽ ጥያቄ ተሰርቶ ካለቀ በኋላ ጥያቄው እንደተጠናቀቀበት ሁኔታ ተመላሽ፣ ውድቅ እና እንዲቆይ የተደረገ የሚል ማህተም ደረሰኞቹ እንዲያርፍባቸው ይደረጋል፡፡ እንዲቆይ ያረፈበትን ደረሰኝ በተመለከተ ምላሽ የሚሰጥ ተቀባይነት ያለው ማስረጃ ከቀረበ የተመላሽ ማቅረቢያ ጊዜው ወይም ቀድሞ የቀረበበት ቀን ተይዞ በድጋሚ የሚጣራና ተገቢው ምላሽ የሚሰጠው ይሆናል፡፡
9. የመደበኛው የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመላሽ ስጋት ተኮር ማድረግ በሚያስችል የአሰራር ስርዓትና የስጋት መምረጫ መስፈርት ማኑዋል መሰረት ተግባራዊ ይደረጋል፡፡
10. ከሐምሌ 1 ቀን 2017 ጀምሮ ተፈጻሚ በተደረገው የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 1395/2017 የጥሬ ገንዘብ ግብይት ገደብ መሠረት ከ 50,000 (ሀምሳ ሺህ) ብር በላይ የያዘ ለታክስ ተመላሽ የሚቀርቡ የግብይት ደረሰኞች ከተጠቀሰው ገንዘብ በላይ በጥሬ ገንዘብ የተከፈለ ከሆነ የታክስ ተመላሽ ጥያቄ ተቀባይነት አይኖረውም፡
11. በታክስ ኦዲት፣በኢንቨስትጌሽን ኦዲት፣ በአገልግሎት ኦዲት እና በሌሎች የስራ ክፍሎች የሚወጡ የተመላሽ ውሳኔውን የማጣራትና የማረጋገጥ ስራው በዚህ መመሪያ በተገለጸው አግባብ መሰረት ተከናውኖ የተመላሽ ውሳኔው ማውጣት አለበት፡፡
12. የተመላሽ ጥያቄ አቀራረብን በተመለከተ በኤሌክትሮኒክስ የተዘጋጀውን ተመላሽ መጠየቂያ ሲስተም በመጠቀም ወይም የፀደቀውን ቅፅ ሞልቶ ማቅረብ ይጠበቃል፡፡
13. ለተመላሽ ክፍያ የሚውል ገንዘብ በወሩ ከተሰበሰበው አጠቃላይ የተጨማሪ እሴት ታክስ ገቢ 10 በመቶ በመቀነስ መያዝ ይኖርበታል፡፡
14. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 13 የተገለጸው ለተጨማሪ እሴት ታክስ ተመላሽ ከተሰበሰበው ተቀንሶ የተያዘው የገንዘብ መጠን በተሻሻለው የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 1395/2017 የአዋጅ ቁጥር 979/2008 አንቀጽ 89(2)(ሐ) ተመላሽ ለሚደረግ የንግድ ትርፍ ግብር ጥቅም ላይ ይውላል፡፡

14/ <u>ዘግይቶ በተከፈለ የተመላሽ ሒሣብ ላይ ስለሚከፈል ወለድ</u>

1/ በዚህ መመሪያ አንቀፅ 4፣ 5 እና 6 በተደነገገው መሰረት የታክሱ ባለስልጣን የተመላሹን ሒሣብ ያልከፈለ ከሆነ፣ የተመላሹ ሒሣብ መከፈል ከነበረበት

አግባብነት ካለው ጊዜ መጨረሻ ጀምሮ ተመላሹ ሒሣብ እስከተከፈለ ድረስ ላለው ጊዜ የታክሱ ባለስልጣን ወለድ መክፈል አለበት፡፡

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሚከፈለው ወለድ ምጣኔ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ከተመለከተው ጊዜ በፊት ባለው የሩብ ዓመት በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙ ባንኮች የንግድ ብድር የሚሰጡበት ከፍተኛው የወለድ ምጣኔ ይሆናል፡፡

3/ በዚሁ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 እና 2 ለተገለፀው አፈፃፀም ወለዱን ለመክፈል አግባብ ላለው ፍ/ቤት ቀርቦ የተሰጠ ውሳኔ ማስረጃ በማያያዝ ውሳኔው በተሰጠበት በ6 ወራት ጊዜ ውስጥ መቅረብ አለበት፤በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ ያልቀረበ ጥያቄ መብቱ እንደተወ ይቆጠራል፡፡

ክፍል ስድስት

ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

15. የታክስ ባለስልጣኑ ኃላፊነት

የተፋጠነ ቀረጥ ተመላሽ ስርዓት ተጠቃሚዎች ያቀረቡትን ሪፖርት በማጠናቀር በየስድስት ወሩ ለኢንዱስትሪ ሚኒስቴር እና ለገንዘብ ሚኒስቴር ሪፖርት ያቀርባል፡፡

16. ስለተሻሩ መመሪያዎች

1/ የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመላሽ አፈጻፀም መመሪያ በገቢዎች ሚኒስቴር በተመዘገበ ቁጥር 148/2011 ወይም በፍትሕ ሚኒስቴር የተመዘገበበት ቁጥር 164/2013 በዚህ መመሪያ ተሽሯል፡፡

2/ ከተጨማሪ እሴት ታክስ ተመላሽ አፈጻፀም ጉዳይ ጋር በተያያዘ ይህን መመሪያ የሚቃረን ማንኛውም መመሪያ ወይም ሰርኩላር ተፈጻሚነት የለውም፡፡

17. የመሸጋገሪያ ድንጋጌ

ይህ መመሪያ ከመውጣቱ በፊት ተጀምረው ውሳኔ ያላገኙ ጉዳዮች በተሻረው መመሪያ መሠረት ውሳኔ ያገኛሉ፡፡

18. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ በፍትህ ሚኒስቴር ተመዝግቦ፤ በገቢዎች ሚኒስቴር ይፋዊ ድረ-ገጽ ላይ ከተጫነበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ፤ ሚያዝያ፣ 2018 ዓ.ም

ዓይናለም ንጉሴ አሊ

የገቢዎች ሚኒስቴር ሚኒስትር